የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሦስተኛ ሰበር ሰሚ ችሎት

ሰበር መ/ቁ 239267

ጥቅምት 4 ቀን 2018ዓ.ም

---

**ዳኞች፡-**

አበባ እምቢአለ

ብርሃኑ አመነው

ገበየሁ ፈለቀ

በእዉቀት በላይ

ሰናይት አድነዉ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

**አመልካች፡-** ብርሃነ ንጉስ አበራ

**ተጠሪ፡-** የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የማታለል ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ ተከሳሹ በሁለት ተደራራቢ ወንጀል ድርጊት ሊቀጣ የሚችል መሆን አለመሆኑን ይመለከታል፡፡ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 03 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 223511 ጥቅምት 1 ቀን 2015 ዓ.ም

በዋለዉ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 234178 ጥቅምት 09 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ 9 ክሶችን ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም ፡-

1ኛ. የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23(1)(ሐ) በተደነገገው መሰረት አንቀጽ 23(3) በመተላለፍ ሀሰተኛ ስም፣ ሀሰተኛ መታወቂያ፣ ሀሰተኛ ውክልና፣ ሀሰተኛ የባንክ ገንዘብ ወጪ ማዘዣ ተጠቅሞ ታሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንድነት ቅርንጫፍ የባንኩ ደንበኛ የሆኑትን የአቶ ታዬ ማርቆስ ገንዘብ ብር 4,640,437 ሊያወጣ ሲል በባንኩ ሰራተኞች ተደርሶበት እጅ ከፍንጅ የተያዘ በመሆኑ ሐሰተኛ የመንግስት እና ህዝባዊ የግል ድርጅት ሰነድ መገልገል ወንጀል ፈፅሟል፣

2ኛ. የወንጀል ህግ 27(1) እና 692 (1) ድንጋጌ ተላልፎ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ሐሰተኛ ማንነት፣ ሐሰተኛ መታወቂያ፣ ሐሰተኛ ውክልና፣ ተጠቅሞ ከላይ በክስ አንድ የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት ስለፈጸመ የአታላይነት ሙከራ ወንጀል ፈጽሟል፡፡

3ኛ. የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23(2)(ሀ) ተላልፎ ሐሰተኛ ስም ሐሰተኛ ማንነት፣ ሐሰተኛ መታወቂያ እና ሐሰተኛ ውክልና በሐሰተኛ የባንክ ገንዘብ ወጪ ማዘዣ ሰነድ ተጠቅሞ ታህሳስ 03 ቀን 2011 ዓ/ም የአቶ መለሰ ሲሳይን ገንዘብ ብር 1,650,000 ወጪ አድርጎ ስለተሰወረ ሐሰተኛ የመንግስት እና የሕዝባዊ ሰነድ መገልገል ወንጀል ተፈጽሟል፣

4ኛ. የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1) ድንጋጌን ተላልፎ ሐሰተኛ ምንነት፣ ሐሰተኛ መታወቂያ፣ ሐሰተኛ ውክልና ሐሰተኛ የባንክ ገንዘብ ወጪ ማድረጊያ ሰነድ ተጠቅሞ ከላይ በክስ 3 የተመለከተውን ወንጀል በመፈጸም የአታላይነት ወንጀል ፈፅሟል፣

5ኛ. የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23(2)(ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት አስቦ ሐሰተኛ የባንክ ደብተር እና ሐሰተኛ መታወቂያ በመያዝ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አፍሪካ ጎዳና ቅርንጫፍ በመቅረብ የባንኩ ደንበኛ የሆኑትን ሁሴን በደዊ ነኝ በማለት ህዳር 14 ቀን 2011 ዓ/ም ከሒሳባቸው ብር 230,000 ወጪ አድርጎ የተሰወረ በመሆኑ ሐሰተኛ የመንግስት እና የህዝባዊ ድርጅት ሰነድ መገልገል ወንጀል ፈጽሟል፣

6ኛ. የወንጀል ህግ ቁጥር 692(1) ድንጋጌ በመተላለፍ ሐሰተኛ ሰነድ ተጠቅሞ ከላይ በክስ አምስት የተመለከተውን ወንጀል በመፈጸም የማታለል የወንጀል ተግባር ፈጽሟል፣

7ኛ. የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 23(2)(ሀ) ተላልፎ ሐሰተኛ መታወቂያ፣ሐሰተኛ ማንነት፣ ሐሰተኛ የባንክ ደብተር እና ሐሰተኛ የባንክ ገንዘብ ወጪ ማዘዣ ተጠቅሞ የባንኩ

ደንበኛ የሆኑትን የአቶ ገ/ጻዲቅ ኃይሉን ብር ታህሳስ ወር 2011ዓ/ም በተለያ ቀናት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቢሸፍቱ እና ዱከም ቅርንጫፍ በጠቅላላው ብር 1,310,000 ወስዶ የተሰወረ በመሆኑ የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀል ፈጽሟል፤

8ኛ. የወንጀል ህግ 692(1) ድንጋጌን ተላልፎ ከላይ በክስ 7 የተመለከተውን የማታለል ወንጀል ፈጽሟል፡፡

9ኛ. የወንጀል ህግ ቁጥር 385 ድንጋጌን በመተላለፍ ከላይ የተመለከቱትን ሁሉንም የወንጀሎች ድርጊቶች ለመፈጸም ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት የመገልገል ወንጀል ፈጽሟል የሚሉ ክሶች ቀርበውበታል፡፡

አመልካች የቀረበበትን ክስ በመቃወም ክዶ የተከራከረ ቢሆንም ጉዳዩን የተመለከተው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዘጠኙም ክሶች ጥፋተኛ በማለት 13 ዓመት ጽኑ እስራት እና ብር 10,000 (አስር ሺህ) እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረበውን ይግባኝ ተመለከተው የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ አጸንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ አቤቱታ ያቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የሰበር የቅሬታ ነጥቦች አመልካች ላይ ቀርበው የነበሩት ዘጠኝ ክሶች ተጣምረው አለመቅረባቸውና በዘጠኙም ክሶች ጥፋተኛ መባሌ ስህተት ነው ምክንያቱም በአንቀጽ 61 ስር በግልፅ በአንድ በተጠበቀ መብት ላይ የሚደረጉ ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ ወንጀሎች የተደረጉት በአንድ ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ከሆነ እና ድርጊቶቹም በሙሉ በአንድ ድርጊት ስር የሚሸፈኑ ከሆነ ተከሳሹ ሊከሰስ የሚገባው በአንድ ክስ ስለመሆኑ የተደነገገ መሆኑ፤ክሱ ሊቀርብብኝ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32 መሰረት እንጂ የተለያየ ዘጠኝ ክስ ሊቀርብብኝ አይገባም፤ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 699 በሙስና ወንጀል ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የለውም፤ በሰ/መ/ቁ 104637 መሰረት ከባድ የማታለል ወንጀል የተፈፀመው ሀሰተኛ ሰነድ ተገልግሎ ቢሆንም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 61 መሰረት ሊጠየቅ የሚገባው በአንድ ክስ መሆኑን አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶበታል፤ በንግድ ህጉ አንቀጽ 896 መሰረት የግል ተበዳይ ባንኩ እንጂ ደንበኞቹ አይደሉም፤ የግል ተበዳይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመሆኑ 1ኛ፣ 3ኛ፣ 5ኛ እና 7ኛ ክሶች ሀሰተኛ ህዝባዊ ሰነድ መገልገል ተብሎ አንድ ክስ እንዲሁም 2ኛ፣ 4ኛ፣ 6ኛ፣ እና 8ኛ ክሶች ማታለል ፈጽሟል ተብሎ አንድ ክስ በድምሩ ሁለት ክስ ተጠቃሎ መቅረብ ነበረበት፤ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክሶችን የተከላከልኩ ስለሆነ በነፃ ልሰናበት፤የጥፋት መደቡ ዝቅተኛ ሊሆን ይገባል ፣ ልዩ ማቅለያ ያቀረብኩት አለመያዙ ትክክል አይደለም የሚሉ ናቸዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም ተመርምሮ አመልካች በአንድ የወንጀል ድርጊት በፀረ ሙስና አዋጅ 881/2007 እና በወንጀል ህጉ በተደራቢነት መቀጣታቸው ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ታዞ መልሱን አቅርባል፡፡

ተጠሪ በቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው መልስ ሀሰተኛ ሰነድን ማዘጋጀትንና መገልገልን በተመለከተ (ክስ 1፣4፣5 ና 6) ፡- ድርጊቶቹ የተፈፀሙት በተመሳሳይ ሁኔታ አይደለም፤ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ የተለያዩ ጥበቃ ያላቸውን መብቶች በመፃረር በተለያዩ መሠረታዊ አዳዲስ ወንጀል የማድረግ ሀሳቦች ጭምር የተፈጸሙ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ 60(ሀ)(ሐ) እና 62 መሠረት እንዲሁም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61 ተቃራኒ ንባብ መሠረት በተደራራቢነት ጥፋተኛ መባላቸው እና መቀጣታቸው ተገቢ ነው፤የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61ን ሁኔታዎች የሚያሟላ አይደለም፤ የወንጀል ሕጉን በመተላለፍ የአታላይነት ወንጀል መፈጸም ተደራራቢ ክሶችን በተመለከተ (2፣4፣6 እና 8ኛ ክሶች)፡- በወንጀል ህጉ 699 ማናቸውም ዓይነት የማታለል ተግባር የተፈጸመው ወደ ሐሰተኛነት በተለወጠ ሰነድ አማካኝነት ሲሆን አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ በሚል በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ እና ይህ የሕጉ ልዩ ክፍል ከወንጀል ሕጉ አጠቃላይ መርህ በላይ ገዢ በመሆኑ አመልካች በተደራራቢነት መቀጣታቸው ተገቢ ነው፤ የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 ከወንጀል ሕጉ በኃላ የወጣ ቢሆንም አንቀጽ 699 የሚገኘው በልዩ ክፍል በመሆኑ ለሙስና ወንጀሎች ጭምር ገዢ መሆኑን፤ 9ኛ ክስ መታወቂያ ሀሰተኛ ማዘጋጀት ጋር በተያያዘ ከልዩ ባህሪው በመነሳት ክሱ የቀረበው ሀሰተኛ መታወቂያዎችን በተለያዩ ቀበሌዎችና ሀሰተኛ ማንነቶችን ጭምር በማዘጋጀቱ እና በመገልገሉ ተነጥሎ በአንቀጽ 385 የቀረበ ክስ በመሆኑ ከ1ኛ -8ኛ ካሉ ክሶች ጋር ተመሳሳይ አይደለም፤ የሰበር ውሳኔ በሰ/መ/ቁ/104637 እና በቅርቡ የተወሰነው 232750 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የላቸውም ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ሀሰተኛ ሰነዶች ማዘጋጀትና መገልገልን በተመለከተ ድርጊቱ በተለያዩ መብቶች (ተቋማት ጭምር) በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ሰነዶች በተለያዩ ሀሰተኛ ስሞች እና ሁኔታ እንዲሁም በተለያዩ አዳዲስ ወንጀል የማድረግ ሀሳቦች የተፈጸሙ በመሆኑ በቀጥታ ከወንጀል ህጉ 61 ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን አምስት ዳኞች የተሰየሙበት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ጋር መርምሮ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 104637፤ 232750 እና 107195 ላይ በተመሳሳይ የወንጀል ጉዳይ የወንጀል ህግ ቁጥር 61(3)ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ለአንድ ወንጀል ጥፋት ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባዉ አንድ ቅጣት

ነዉ፤የማታለል ወንጀል የተፈጸመዉ ዋናዉን ወንጀል ከግብ ለማድረስ በአንድ ወንጀል መስራት ሃሳብ የተፈጸመ ወንጀል ድርጊት ነዉ የሚል ይዘት ያለዉ አስገዳጅ ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን በሌላ በኩል በሰበር መ/ቁ 76773 እና ሰበር መ/ቁ 85237 ላይ ደግሞ በወንጀል ህግ ቁጥር 699 መሰረት በሁለቱም ድንጋጌዎች ጥፋተኛ መሰኘት አለበት በማለት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሌላ አስገዳጅ ሰበር ዉሳኔ መስጠቱን እና የሰበር ችሎቱ ዉሳኔዎች የሚቃረኑ መሆኑን በመገንዘብ እነዚህ ሁለት ዓይነት ዉሳኔዎች የሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔዎች ተገማች ፤ተአማኒ እና አንድ ዓይነት እንዳይሆኑ የሚያደርግ ስለሆነ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት ትርጉም እንዲሰጥበት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26(1) መሰረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በማቅረቡ ፕሬዚዳቱ በሰባት ዳኞች እንዲታይ መርተዋል፡፡

በተያዘዉ ጭብጥ ላይ ግራቀኙ የበኩላቸዉን መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡በአቃቤ ህግ በኩል የቀረበዉ መከራከሪያ ባጭሩ ሲታይ ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል በተመለከተ የወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል አንቀጽ 699 መሰረት አግባብነት ያለዉ ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ እንደሚሆን ስለተደነገገ ሰበር ችሎቱ በዚህ አግባብ የሰጣቸዉ ዉሳኔዎች ገዥ ሊሆኑ ይገባል የሚል ሲሆን በአመልካቹ ጠበቃ በኩል የቀረበዉ መከራከሪያ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(1/3) አተገባበር እና ትርጉም ጋር በተያያዘ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 107195 ላይ በተሰጠዉ ትርጉም መሰረት በሰባት ዳኞች ታይቶ ቢወሰን ፍትህ ያረጋግጣል የሚል እምነት እንዳላቸዉ ገልጸዋል፡፡

ጉዳዩም በሰባት ዳኞች እንዲታይ ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ አመልካቹ ሀሰተኛ ስም፤ሀሰተኛ መታወቂያ፤ሀሰተኛ ውክልና፤ ሀሰተኛ የባንክ ገንዘብ ወጪ ማዘዣ ተጠቅሞ በተለያዩ ሰዎች ስም ያለ የባንክ ሂሳብ (አካዉንት) ላይ በተለያዩ ቀናት የተለያየ መጠን ያለዉ ገንዘብ ወጭ አድርጓል በሚል የተከሰሰ ሲሆን ለዚህም ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል እንዲሁም በማታለል ወንጀል በተደራራቢነት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱን መዝገቡ ያሣያል፡፡በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጡት ፍሬነገሮች አንጻር ሲታይ የማታለል ወንጀል የተፈጸመዉ ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በመገልገል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡አከራካሪ የሆነዉ ጉዳይ በዚህ አይነት የወንጀል ድርጊት ላይ ተከሳሹ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል ወንጀል እና በማታለል ወንጀል በተደራቢነት ጥፋተኛ መባሉ ተገቢ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉ ሲሆን በዚህ ረገድ ሰበር ችሎቱ በተለያዩ መዝገቦች የሰጠዉ ዉሳኔ አቋም በሁለት ተከፍሎ ሊታይ የሚችል ነዉ፡፡

አንደኛዉ ሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ 76773 እና ሰበር መ/ቁ 85237 የሰጠዉ ዉሳኔ የሚመለከት

ሲሆን በእነዚህ እና ሌሎች መሰል መዝገቦች ላይ የተረጋገጠዉ ፍሬነገር ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በመገልገል የማታለል ወንጀል መፈጸም ሲሆን ጉዳዩን ከወንጀል ህግ አንቀጽ 61(3) እና 699 ድንጋጌዎች አንጻር በመመርመር በማታለል ወንጀል እና ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል አግባብነት ባለዉ ድንጋጌ መሰረት በሁለት የተለያዩ ድንጋጌዎች (በተደራቢነት) ጥፋተኛ መባል አለበት የሚል አቋም የተንጸባረቀበት ነዉ፡፡በሁለተኛዉ ጎራ ደግሞ ሰበር መ/ቁ 104637፣107195፣232750 እና 234082 እንዲሁም መሰል መዝገቦች ላይ የተሰጠ ዉሳኔ የሚመለከት ሲሆን በእነዚህ መዝገቦች ላይ በፍሬነገር ደረጃ የማታለል ድርጊት የተፈጸመዉ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል መሆኑን ተቀብሎ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ዋናዉ ግብ የሆነዉ ገንዘብ ጥቅም ለማግኘት በአንድ ወንጀል ማድረግ ሀሳብ የተደረገ ነዉ በሚል የወንጀል ህጉን አንቀጽ 61(3) ምርኩዝ በማድረግ በማታለል ወንጀል ብቻ ጥፋተኛ ሊባል ይገባል እንጂ በተደራቢነት ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም መገልገል ሊጠየቅ አይገባም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡በመዝገቦቹ ላይ በተደረገዉ ክርክር የተረጋገጠዉ ፍሬነገር ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀት እና/ወይም በመገልገል የንብረት ወይም ገንዘብ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ የማታለል ወንጀል የተፈጸመ መሆኑ ሲሆን አድራጊዉ በማታለል ወንጀል እና ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም መገለገል በተደራቢነት መቀጣት ወይም በመሰረታዊዉ ወንጀል ብቻ ተጠቃሎ መቀጣት አለበት የሚለዉን የህግ ክርክር በተመለከተ ሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ሲታይ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የአቋም ልዩነት ወይም አንጻራዊ ግጭት መኖሩ ተስተዉሏል፡፡

የሰበር ችሎት ዋነኛ ሃላፊነት ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጎም ወይም የህግ አተገባበር ስርዓት ማረጋገጥ እና ተገማች የሆነ ዳኝነት አገልግሎት እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡ከዚህ አኳያ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በፍርድ ቤቶች ወይም በችሎቶች መካከል የሚታዩ የህግ አተረጓጎም ወይም አተገባበር ልዩነነት መከሰቱ የሚያስከትለዉ ጉዳት ከፍተኛ ስለሚሆን ማረቅ አስፈላጊ ነዉ፡፡በተያዘዉ ክርክር ከላይ እንደተገለጸዉ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የተፈጸመ የማታለል ወንጀል ጋር በተያያዘ የማታለል ወንጀል እና ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል በተደራራቢነት የሚያስቀጣ መሆን አለመሆኑ ላይ በሰበር ችሎቱ ዉሳኔዎች መካከል የአቋም ተቃርኖ መኖሩ እዉን እንደመሆኑ ይህንን ተቃርኖ ለመፍታት የህጉን ይዘትና ዓላማ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

የወንጀል ህግ ዓላማ፣ግቡ እና አፈጻጸሙን የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች በጠቅላላ ክፍል የተደነገጉ ሲሆን ልዩ ልዩ ክፍሉ ደግሞ የወንጀል ፍሬነገር የሚያቋቁም ድርጊትን ወይም አልድርጊትን እና ቅጣቱን በመዘርዘር ተደንግጓል፡፡በወንጀል ህጋችን ጠቅላላ ክፍል ከተደነገጉት መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱ ስለተደራራቢ ወንጀል ምንነት እና ተጠያቂነት የሚመለከት

ነዉ፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 60 እንደተደነነገዉ ተደራራቢ ወንጀሎች ተደርጓል የሚባለዉ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ አንድ ዓይነት ወይም የተለያዩ ማናቸዉም ዓይነት ግዙፍነት ያላቸዉ ወንጀሎችን አከታትሎ ማድረግ ወይም በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከለሁለት በላይ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ወይም በአንድ ድርጊት ልዩ ልዩ ጊዙፋዊ ዉጤት የሚያስከትሉ ወንጀሎችን መፈጸም ወይም አንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ያደረገዉ ወንጀል አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸዉ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ በማለት ትርጉም ሰጥቷል፡፡ይሁንና የህጉ አቀራረጽ እና ይዘት ጥቅል ሆኖ ጥልቅ የህግ ጽንሰ ሀሳብ የያዘ በመሆኑ አረዳድ እና አተገባበሩ ላይ ባበለሙያዎች መካከል የሃሳብ ልዩነት መኖሩ እሙን ነዉ፡፡

በ1949ዓ.ም የወጣዉ የሀገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ (ነጋሪት ጋዜጣ ቁጥር 1/1954ይመለከታል) ላይ ማብራሪያ የጻፉት **ፌልፐ ግራቨን** ሀሳቡን ከተለያዩ ሀገሮች ህግ ጋር በማነጻጸር ለማስረዳት የሞከሩ ሲሆን እሳቸዉ እንደገለጹት«**concurrence comes in to being either when several unlawful acts are done in contravention of one or more articles of the law (concurrence of offences,or material concurrence ) or when one unlawful act is done in contravention of several articles of the law (concurrence of provisions or notional concurrence).**እንደሆነ ያስረዳሉ።ይህ በግርድፉ ወደ አማርኛ ስመለስ ተደራራቢ ወንጀል አለ ለማለት የሚቻለዉ ተለያዩ ህገወጥ ድርጊቶች ማድረግ እንድ ወይም ከአንድ በላይ ህግ ድንጋጌ መጣስ ያስከተለ እንደሆነ (ቁሳዊ/ግዙፋዊ መደራረብ ) ወይም አንድ ህገወጥ ድርጊት ከአንድ በላይ የሆነ የህግ ድንጋጌ መጣስ ያስከተለ እንደሆነ (ጣምራ /ህጋዊ መደራረብ) ተብሎ እንደሚከፈል ፤ሌላዉ የህግ ባለሙያ የሆኑት ደጀኔ ግርማ (ዶ/ር) ተደራራቢ ወንጀልን ሲገልጹ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የወንጀል ድርጊቶችን በአንድ ጊዜ ወይም በአንድ ዓይነት ሁኔታ ዉስጥ የሚፈጸም መሆኑን (concurrent crimes could understood as two or more crimes that are commited in the same transction or situation ) እነዚህ ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑት ወንጀሎች የተፈጸሙት በተለያየ ጊዜ ወይም ሁኔታዎች ዉስጥ ከሆነ ወንጀሉ ተደራራቢ ወንጀል ሳይሆን ተከታታይ(consecutive crimes) ወንጀል ይሆናሉ ብለዋል። ሌሎችም ጸሃፊዎች ድንጋጌዉን በተለያየ አገላለጽ ለማብራራት የሞከሩ ሲሆን ተደራራቢ ወንጀል የተገለጸበት አግባብ የቀድሞ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ (1949) እና አሁን ስራ ላይ ባለዉ ወንጀል ህግ (1996) መካከል ልዩነት መኖሩን ልብ ይለዋል።የሆነ ሆኖ ተደራራቢ ወንጀል መኖር አለመኖሩን ለመለየት የተፈጸመዉን

ድርጊት፤ድርጊቱ የተፈጸመበት ሀሳብ፤ድርጊቱ ያስገኘዉ ዉጤት እና የህጉን ይዘት ማገናዘብ አስፋላጊ ነዉ።

የኢፊዲሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60 ንኡሳን ድንጋጌዎች አንጻር ተደራራቢ ግዙፍ ወንጀሎች ተፈጽሟል ለማለት የሚቻለዉ ድርጊቱ በተለያዩ የወንጀል ህግ አንቀጾች ስር የሚያሲቀጡ፤ልየ ልዩ የወንጀል ድርጊቶች መፈጸማቸዉ ሲረጋገጥ ወይም ድርጊቶቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም እንደአንድ ወንጀል ድርጊት መቆጠራቸዉና በአንድ ድንጋጌ ስር ማስቀጣታቸዉ ቀርቶ እያንዳንዱ ተመሳሳይ ድርጊት እንደአንድ ወንጀል ተቆጥሮ በአንድ አንቀጽ በተደራራቢት የሚያስከስስና የሚያስቀጣ እንደሆነ ነዉ።በጥቅሉ ሲታይ ተደራራብ ወንጀል አለ የሚባለዉ አንደኛዉ የተቀላቀሉ ህገወጥ ድርጊቶች አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆነ የህግ ድንጋጌ ተላልፎ ሲገኝ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ አንድ ህገወጥ ድርጊት የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎችን ተላልፎ ሲገኝ ወይም በአንድ ወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት ያደረገዉ ወንጀል አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥሥ ሆኖ ቁጥራቸዉ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ድንጋገዉ ያስገነዝባል፡፡የ1996"ቱ የወንጀል ህግ (አዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 60 ይመለከታል)

በሌላ በኩል ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት የሚለዉ መርህ በአንቀጸግ 61 ስር ተደንግጓል፡፡ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት የሚለዉ መርህ ተደራራቢ ወንጀል መኖርን ታሳቢ ያደረገ ነዉ፡፡የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61 መሰረታዊ ይዘት ሲታይ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት (unity of guilty and unity of penality) የሚለዉ መርህ ተግባረዊ ለማድረግ እንደመሰረታዊ መመዘኛ የሚወሰዱት፤አድራጊዉ ድርጊቶቹን ደጋግሞ ወይም አከታትሎ መፈጸሙ፤የወንጀል ድርጊቱ በአንድ መብት ወይም ጥቅም ላይ መፈጸሙ፤ድርጊቱ በአንድ ወንጀል ከመስራት ሃሳብ የመነጨ መሆኑ እና ድርጊቱ አንድ ዓላማ ለማሳካት መፈጸሙ ሲረጋገጥ መሆኑን ያሣያል፡፡በተለይም በአንቀጽ 61(1)ላይ እንደተደነገገዉ በህግ በተጠበቀ በአንድ መብት ላይ የሚደረጉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የተቀላቀሉ የወንጀል ድርጊቶች የተደረጉት በአንድ የወንጀል ማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ሲሆን እና ድረጊቶቹ በሙሉ በአንድ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑ ሲሆን አድራጊዉ ተመሳሳይ ባህርይ ባላቸዉ በሁለት ወይም ከሁለት በበለጡ ተደራራቢ የቅጣት ድንጋጌዎች አይቀጣም ይላል፡፡

በዚህ መዝገብ የተያዘዉ ክርክር ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በመገልገል የማታለል ወንጀል ድርጊት ተፈጽሞ ሲገኝ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(3) እና 699 ተፈጻሚነትና አተገባበር ላይ ያለዉን የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ አቋም ልዩነት ማስታረቅ ዓላማ ያደረገ በመሆኑ ከዚሁ አንጻር ብቻ ህጉን መቃኘቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ለዚህ ዓላማ ሲባል የድንጋጌዎቹን ሙሉ ይዘት

መመልከት ይገባል፡፡

የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(3) የድንጋጌ እንደሚከተዉ ይነበባል፡

‹‹አድራጊው የተወሰነ ወንጀል ለማድረግ ሀሳብ ዓለው ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ በተለይም የማይገባው ብልጽግና ለማግኘት በንብረት ላይ ወንጀል አድርጎ እንደሆነ ወይም የሐሰት ገንዘብ ሰርቶ እንደሆነ ወይም ይህንኑ ገንዘብ እንዲዘዋወር አድርጎ እንደሆነ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ ሠርቶ ወይም ተጠቅሞበት እንደሆነ የመጀመሪያ ጥፋት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ሲል መሠረታዊ ከሆነው ወንጀል በኋላ አከታትሎ ያደረገው ድርጊት ከቀድሞ ሀሳቡና ሊደርስበት ካቀደው ግቡ ጋር የተያዘ ሆኖ በዋና ወንጀል ይጠቃለላል››ይላል፡፡በሌላ በኩል የወንጀል ህጉ አንቀጽ 699 በሐሰተኛ ሰነድ ማታለል በሚል ርእስ ስር ‹‹ ማናቸውም ዓይነት የማታለል ተግባር የተፈፀመው ወደ ሐሰተኛነት በተለወጠ ሰነድ አማካይነት ሲሆን አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ በማለት ደንግጓል፡፡

ለተያዘዉ ክርክር መሰረቱ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት ተብሎ በወንጀል ህጉ በጠቅላላ ክፍል የደነገገዉ መርህ እና ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የማታለል ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ አግባብነት ያለዉ ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናል የሚለዉ የወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል ድንጋጌ አተገባበር ጋር በተያያዘ የሰበርችሎቱን አቋም ይመለከታል፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ ሰበር ችሎቱ በሰበር መ/ቁ 76773 እና ሰበር መ/ቁ 85237 የሰጠዉ ዉሳኔ ሀሰተኛ ሰነድ በማዘጋጀትና በመገልገል የማታለል ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ በማታለል ወንጀል እና ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀትና መገልገል አግባብነት ባለዉ ድንጋጌ መሰረት በሁለት የተለያዩ ድንጋጌዎች (በተደራቢነት) ጥፋተኛ መባል አለበት የሚል አቋም የተወሰደበት (ወንጀል ህግ አንቀጽ 61(3) እና 699 ድንጋጌ) መሰረት ያደረገ ሲሆን በሌሎች መዝገቦች ላይ ሰበር ችሎቱ በሰጠዉ ዉሳኔ እንደተመለከተዉ ሀሰተኛ ሰነድ የሥራ ሰው ካልተጠቀመበት በወንጀሉ ያቀደው ዓላማ ከግቡ ሊደርስ የማይችል በመሆኑ ምክንያት ተከታትለው የተፈፀሙ አድራጎቾች በአንድ ወንጀል ማድረግ ሀሳብ እንደተፈጸሙ ተቆጥረው በዋና ወንጀል እንደሚጠቃለሉ እና አድራጊው የሚቀጣው በአንድ ወንጀል መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 109152 (ቅጽ 20) ፤ በሰበር መዝገብ ቁጥር 104637 (ቅጽ 21) እና በሌሎች መዛግብት የተሰጠ ፍርድ ያሣያል፡፡በሁለተኛዉ አቋም ሰበር ችሎቱ ለዉሳኔዉ የሰጠዉ ምክንያት ተጠቃሎ ሲታይ ወንጀል አድራጊዉ ሀሰተኛ ሰነድ የተጠቀመው ዋና ግብ የሆነውን ንብረት የማግኘት ዓላማውን ከዳር ለማድረስ በሆነ ጊዜ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል እና ከባድ አታላይነት ወንጀሎች በመፈጸም ተከሶ ከሆነ ሀሰተኛ ሰነድ ተገልግሏል በሚል የተከሰሰበት ወንጀል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 61(3) መሰረት በወንጀል ሕግ

አንቀጽ 696(ሐ) ሥር ተጠቃሎ ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ይገባል እንጂ በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ አይቀጣም የሚል ነዉ፡፡
በወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(3) ድንጋጌ ስር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ መሰረታዊ ወንጀሎች የተባሉት"... **የማይገባዉን ብልጽግና ለማግኘት በንብረት ላይ የሚፈጸም ወንጀል ወይም የሀሰት ገንዘብ መስራት ወይም ይህንኑ እንዲዘዋወር ማድረግ ወይም ሀሰተኛ ሰነድ መስራት ወይም መጠቀም** (ሰረዝ የተጨመረበት) የሚል ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የማታለል ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ በተደራቢነት ያሥቀጣል የሚለዉ አንቀጽ 699 መደንገጉ ሲታይ ለሰነዶች የተለየ ትኩረትና ጥበቃ ማድረጉን ያመላከታል፡፡እንደሚታወቀዉ ማታለል ተግባር የሚፈጸመዉ በድርጊት፣ በንግግር ወይም በሰነድ ሊሆን ይችላል፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ ማንም ሰዉ ያልተገባ ብልጽግና ለማግኘት በማሰብ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል መሰረታዊ የሆነዉን የማታለል ወንጀል የሰራ እንደሆነ ዓላማዉ እና ግቡ የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት መሆኑ የሚገመት ቢሆንም በአንቀጽ 61(3 )ስር በተደነገገ አግባብ በዋና ወንጀል የሚጠቃለል መሆኑ ቀርቶ በአንቀጽ 699 በተደነገገዉ አግባብ ሀሰተኛ ሰነድ በተመለከተ አግባብነት ያለዉ ድንጋጌ በተደራቢነት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡
ወንጀል ህጋችን በዚህ አግባብ በተደራቢነት ቅጣት የሚያስቀጡ ወንጀሎች አስመልክቶ ተደንግጎ የሚገኘው ይኸው አንቀጽ 699 ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በኮምፒውተር አማካኝነት የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተመለከተ በወንጀል ህጉ ክፍል ሁለት ስር አንቀጽ 710 እና 711 ስር የተመለከቱ ድንጋጌዎች በኮምፒውተር አማካኝነት የሚፈፀም ማናቸውም ዓይነት ወንጀል በዚህ የወንጀል ህግ የሚያስቀጣ ሌላ ወንጀል አስከትሎ እንደሆነ ለዚሁ ወንጀል ተገቢነት ያለው ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ የሚሆን መሆኑን ተደንግጎ ይገኛል፡፡በተመሳሳይ ሁኔታ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነት በገንዘብ መርዳት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 780/2013 አንቀጽ 29(3)መ ላይ ተከሳሹ በአመንጪ ወንጀል ጭምር እንደሚቀጣ ያሳያል፡፡
ከዚህም ሁሉ መረዳት የሚቻለው የማይገባ ብልጽግና ለማግኘት በማስብ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የተደረገዉ ዋና ወንጀል የሆነዉን ግብ ለማስፈጸም ነዉ ተብሎ እንደ አንድ ወንጀል ተቆጥሮ በዋና ወንጀል ተጠቃሎ ያሥቀጣል የሚለዉ አንቀጽ 61(3) ቢኖርም ዋናዉን ወንጀል ከግብ ለማድረስ ሲል አድራጊዉ ሀሰተኛ ሰነድ መገልገሉ ከተረጋገጠ አግባብነት ያለዉ ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ እንደሚሆን በአንቀጽ 699 ላይ በግለጽ የተደነነገ መሆኑን ነዉ፡፡በሌላ በኩል የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61(3) እያለ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 699 የተደነገገበት ዓላማ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 ዓላማ አፈጻጸም ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ተደራርበው የተፈጸሙ የወንጀል

ድርጊቶች በሙሉ በአንድ የወንጀል ድንጋጌ ስር የማይሸፈኑበት ሁኔታ ሲኖር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 ስር የተደነገገው ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት የሚለው መርህ ተግባራዊ እንደማይሆን እና አድራጊው በተደራራቢ, ወንጀሎች ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ለማመላከት በመሆኑ ሁለቱም ድንጋጌዎች የየራሳቸው ዓላማ ያላቸው ድንጋጌዎች እንጂ አንደኛው ሌላውን የሚተካ ወይም አንዱ ጠቅላላ መርህ ሌላው ልዩ ድንጋጌ ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም የሰበር ችሎቱ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል ማታለል ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ አድራጊዉ ዋና ወንጀል በሆነዉ የማታለል ወንጀል ብቻ ይቀጣል የሚለዉ ምክንያትና የህግ አተረጓጎም የወንጀል ህጉን አንቀጽ 699 ድንጋጌ አስፈላጊነት ጥያቄ ዉስጥ ያሥገባል፡፡ይህ የህግ አተረጓጎም አንቀጽ 699 ድንጋጌ ዋጋ አልባ ወይም የማይፈለግ ዉጤት (absured result) እንዲኖረዉ ስለሚያደረግ ተመራጭ የህግ አተረጓጎም ደንብ አይደለም፡፡በመሰረቱ የትኛዉም የህግ ድንጋጌ ምክንያታዊ እና የራሱ ዓላማ አለዉ ተብሎ ግምት ይወሰዳል፡፡ድንጋገጌዉ ራሱን ችሎ የሚቆም እና ግልጽ እስከሆነ ድረስ መርቃማ የህግ አተረጓጎም (Golden Rule ) ደንብ መሰረት እንዳለ ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ዉጤታማና ተመራጭ ያደርገዋል፡፡በሌላ አገላለጽ አድራገዉ የጥፋት ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ ሲል መሰረታዊ ከሆነዉ ወንጀል በኋላ አከታትሎ ያደረገዉ ድርጊት ከቀድሞ ሃሳቡና ሊደርስበት ካቀደዉ ግቡ ጋር የተያያዘ ሆኖ በዋና ወንጀል እንደሚጠቃል እና እንደሚቀጣ ህግ አዉጪዉ እያወቀ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የተፈጸመ ማታለል ወንጀል ሲሆን ግን ሀሰተኛ ሰነድ የሚመለከት ድንጋጌ በተደራቢነት እንደሚያሥጠይቅ መደንገጉ ሲታይ ሀሰተኛ ሰነድ መገለገል የሚፈጸም ወንጀል ጋር በተያያዘ በተደራቢነት እንዲቀጣ የህግ አዉጭዉ ግልጽ ፍላጎት እንዳለዉ እንረዳለን፡፡

ሲጠቃለል የወንጀል ህጉ አንቀጽ 699 በንብረት መብት ላይ የሚፈጸሙ ማታለልን ያካተቱ ወንጀሎች የሚመለከት የህጉ ልዩ ልዩ ክፍል ዉስጥ የሚገኝ እና ግልጽ ድንጋጌ ነዉ፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የማይገባ ብልጽግና (ጥቅም) ለማግኘት በሚል የማታለል የወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ በወንጀል ህጉ ጠቅላላ ክፍል ዉስጥ አንቀጽ 61(3) ጋር በማይቃረን እና በተጣጣመ ሁኔታ ዉጤታማ የህግ አተረጓጎም መርህ መሰረት ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡ስለሆነም ሀሰተኛ ሰነድ በመገለግል የማታለል ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ አድራጊዉ መሰረታዊ ወንጀል በሆነዉ የማታለል ወንጀል እንጂ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል በተደራቢነት ሊቀጣ አይገባም በማለት ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ232750 ፣ 234082፣104637 እና 107195 እንዲሁም ሌሎች መሰል መዝገቦች ላይ የሰጠዉ የህግ ትርጉም የወንጀል ህጉን አንቀጽ 699

ግልጽ ድንጋጌ ዋጋ የሚያሣጣ የህግ አተረጓጎም የተከተለ በመሆኑ መለወጥ ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. ሀሰተኛ ሰነድ በመገለግል የማታለል ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ አድራጊዉ መሰረታዊ ወንጀል በሆነዉ የማታለል ወንጀል እንጂ ሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል በተደራቢነት ሊቀጣ አይገባም በማለት ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ232750፣234082፣104637 እና 107195 እንዲሁም ሌሎች መሰል መዝገቦች ላይ የሰጠዉ የህግ ትርጉም ተለዉጧል፡፡
2. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(3) ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ሀሰተኛ ሰነድ በመገለግል የማታለል ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ አድራጊዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 699 በተደነገዉ መሰረት አግባብነት ያላቸዉ ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናሉ ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

3ኛ/በዚህ መዝገብ የቀረቡት ሌሎች አቤቱታ ነጥቦች ባለአምስት ዳኞች እንዲታይ መዝገቡ ተመልሷል፡፡